# <u>የዓይጥ ምስክሩ ድንቢጥ--የዶክተር ጌታቸው በጋሻው አዲስ ቅሌት</u>

አሀዱ ዮሐንስ

ዶክተር ጌታቸው በጋሻውና ጭፍን ተከታዩ አበራ ሲሳይ የሚባሉ በቅርቡ በደርግና ግንቦት 7 አዳናቂ ፓል ቶክ ብቅ ብለው ዓለም ያወቀውን የተነቃበትን የግንቦት 7 ውሸት ሀቅ ነው ወገኖች ብለው ሊያሳምኑን ሲለፈልፉ አድምጠናል ። በጣም ያሳዝናል ። ዶክተር ጌታቸው ከዚህ በፊት ቅሌት በቅሌት ሆነው ከዚሁ ተምረዋል የሚል ግምት ነበረኝ ። አዛውንቱ ግን ውሸቴን ብተው ያሽመድምደኝ ያሉ ይመስላል ።

ወደ ግለሰቦቹ ማንነት ከመግባቴ በፊት የብርሃኑ ነጋ ጦር ተብዬ መቀለጃ ከሐሬና ኤርትራ ገና ነቅነቅ አለማለቱን ላስረግጥ ። በጥቂት ቀናት ከኤርትራ ድንበ ተወንጭፎ አዘዞ (ጎንደር ዙሪያ) ደረሰ የተባለው ጦር ያደረገው እንቅስቃሴ ወይም ጦርነት የለም ። በወልቃይት ጠገዴ አርማጨሆ ሀገሬው የወያኔን መስፋፋት በመቃወም ብልጭ ድርግም የሚል የትጥቅ ተቃውሞ ማድረጋቸው ይታወቃል ። ይህን ትግል ለመርዳት የጣሩ ብዙዎችም አይደሉም ። ወያኔ እያደረሰባችው ያለው ግፍ አልበቃ ብሎ ግንቦት 7ና መሪው ደግሞ ትግላቸውን ነጥቀው ሊነግዱበት ተነስተዋል ።፡አርበኞች ግንባር እንዳይደረጅ ሻዕቢያ መሻጠሩን በተመለከተ ብዙ ተብሏልና (የተስፋዬ ጌታቸውና ሊሎች ግድያ፤የኮልኔል ታደሰ ደብዛ መጥፋት ወዘተ) ጊዜ አላጠፋም ። በወልቃይት ጠገዴ አንዳንድ ሙከራዎች ከነበሩም ይህ ራሱን የኢትዮጵያ እንዳይል የታገደው ግንባር ድሮ ያደረገው እንጂ የግንቦት 7 ተዋጽኦ የለም ። ወልቃይትም ሁመራም፤ጠገዴም መተማም፤ ወዘተ ለዘመዶች መደወል መቻላችን የረሱት ይመስላል ዋሾዎቹ ። ግንቦት 7 በብርሃኑ ሙሉ ቁጥጥር ስር ከገባ በኋላ ኢሳትንም በዚያው ቀይዶ ሲይዝና ለሻዕቢያ ሲያስረክብ የግንቦት 7 ምጽዓተ ደወል በማቃጨሉ ትምክህተኛው ብርሃኑ መዘየድ ነበረበትና ጦርነት ጀመርን ብሎ ከኮለኔል ፍጹምና ሻዕቢያ ጋር ዳያስፖራውን ማታለያ ዘዴ ፈጠሩ ። ብርሃኑም ወደ አስመራ አቀና ። ደ ቀ መዝሙሮቹም ላይመለስ ወደ ትግል ሜዳ ነጎደ ብለው ጮሁ። ብርሃኑ አገስትንም በዚያ ካሳለፈ እውነትም ድፍረት እየጀመረ ነው ማለት ነው ። ሂድ ተመለስ አለኝ ጦሩ ብሎ ይመለሳታል ። ሲመለስ አጫፋሪዎች ሁሉ ምን ይውጣቸው ይሆን? ምን ይዋሹ ይሆን ?

በብርሃኑና በቀይ ሽብርተኞች ፓል ቶክ ዛሬ ተናጋሪው፤አብራሪው፤ መካሪውና ገሳጭ የሆኑት--በይፋ- ሻዕቢያዎች ናቸው ። በግንቦት 7 ስብሰባም --ኤኤፍዲ ትዝ ይላችኋል?-- አዳራሹን የሚሞሉት የሻዕቢያ ኤርትራውያን ናቸው ፤፡ የብርሃኑ ውሸት አጋፋሪ የሆኑትም እነዚሁ የኢሳያስ ጭፍሮች ናቸው ። የደርግ ርዝራዦችም አሉ ። አንዱ ለምሳሌ ህይወታቸውን ለትግሉ የሰጡትና ዘመዶቻቸውን ያጡት አቶ መልኬ መንግስቴን ሊያንቋሽሽ ሲነሳ የደርጉን ሟች ነፍሰ ገዳይ ገዛኸኝ ወርቄን ሳያፍር አወድሷል ። ጸረ ትግልና በተለይም ጸረ ጎንደር የሆኑ ግለሰሰቦች፤የጎንደርን ሕዝብ ትግል ለማደናቀፍ የሚሹ ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው ናቸው ግንቦት 7 ትግል ጀመረ ብለው የሚመሰክሩት ፡፡ ወያኔ ይህን ሁኔታ በሁሉም ፈርጅ ሊጠቀምበት ተነስቷል ። ዶክተር ጌታቸው ባለፈው ለአነግ ጥብቅና ቆመው ሕዝብን እንዳስቆጡ ሁሉ አሁንም ለግንቦት 7 ምስክር ሆነው ራሳቸውን ለሰፊ ትብት ዳርገዋል ። አላሰብኩበትም ቢሉም ወያኔና ሻዕቢያን ጠቅመዋል ። ለአርበኞች ግንባር መቶ ናቅፋ መስጠት የሚቀፈው ኢሳያስ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ከተገኘው ገንዘብ ለግንቦት 7 ግማሽ ሚሊዮን መለገሱ ምንም አይቶ ነው ብሎ መጠየቅ እንኳን አልቻሉም ራሳቸውን የመጠቀ ምሁር ባዩ ዶክተር ጌታቸው ። ደግሞስ ኢስያስን አግንጨው ነበር ብሎ መናገሩ ከመቸ ወዲያ ነው አኩሪ የሆነው ? ፎክተሩን የያዛቸው አባዜ አዋርዶ ሳይጨርስ እንድ ክፉ ቁምጥና የሚገድላቸው አይመስልም ።

በዚህ የውሸት ጎርፍ ውስጥ ነው ዶክተር ጌታቸው በጋሻው እንደ እርጎ ዝንብ ዘው ብለው ቅሌትን የተከናነቡት። ያጀባቸው አበራ ሲሳይ ገሸሽ የሚያደርግና ስርቆትን ሳይቀር (የተዋጣ ገንዘብ፤ ቤተ እስራኤል ነን ማለት ወዘተ) ያሳየ ታሪክ አለውና ከቁም ነገርም አላስገባውም ። ዶክተር ጌታቸው በጋሻው በጎሬ የተወለዱ የነፍጠኛ ልጅ ሲሆኑ እንደዚያ ሻዕቢያ ተስፋዬ ገብረአብ ከኦሮሞም በላይ ኦሮሞ ነኝ ሊሉ የሚዳዳቸው ከበሬታን ያጡ ሰው ናቸው ። በትግል ተሳትፎአቸው ብዙውን

ጊዜ አፍራሽ ነው የሚባልላቸው ዶክተር ጌታቸው 80 በመቶ በላይ አሮሞ ኦነግን ይደግፋል ብለው የቀባጠሩ ናቸው ። ግንቦት 7 ከነ ከማል ገልቹ ጋር ገጠመ ሲባልም ዕጹብ ድንቅ ብለው ከብርሃኑና ጭፍሮቹ ጋር በየስቴቱ ሲዞሩና (ኦነግንም በዚያው እየወረፉ) የከማልን ኢትዮጵያዊነትና የግንባሩንም ፍቱንነት ሲያበስሩ አድምጠናል ። ዶክተር ጌታቸው የዶክተር ብርሃኑ (ሳያስተምርና በስፋት ሳይጽፍ ፕሮፌሰር ሆነ የሚለውን እኔ አልቀበለውም ) ደጋፊ የሆኑት እውን አምነውበት ነው ወይስ ዕዝ መጥቶባቸው ብለው የጠየቁ ወገኖች አልጠፉም ። ዶክተር ጌታቸው የዶክተር ነጋን እንቅስቃሴ በመደገፍ በአሜሪካ ብዙ ቦታዎች ዞረዋል ። ከቅርብ ወዲህ ደግሞ የሻዕቢያ ዋና ደጋፊ ሆነው (ኢሳያስን ዩኒቨርስቲ ሳለ አውቀዋለሁ የሚል ውሸትንም አስደምጠውን) ሲናገሩ ሰምተናል ። ዶክተር ጌታቸው የግንቦት 7 የፕሮፓጋንዳ አካል ናቸውና ዋናውን ጉዳይ ለማደናገር የቤት ስራ ተሰጧቸዋል ። ዋናው አወዛጋቢ ጥያቄ የግንቦት 7 ጦር የለም፤ያለው የአርበኞች ግንባር ጥቂት ሀይል ነው፤ይህም ወደ ኢትዮጵያ ምድር አልገባም፤ የግንቦት 7 ወታደራዊ እንቅስቃሴም ሀሰት ነው የሚለው ሆኖ ሳለ ዶክተር ጌታቸውና ሌሎች የዶክተር ብርሃኑ ጀሌ ምሁሮች ደግሞ ከሻዕቢያ ተረድቶ ወያኔን መታገል ይገባል ይቻላል ወይስ ከንቱ ነው ወደሚል ጉንጭ አልፋ ክርክር ሊቀይሩት ይጥራሉ ፡፤ ለነገሩ ዕቅጩን ልንገራቸውና በሻዕቢያ ተረድቶ ኢትዮጵያን መጥቀም አይቻልም ።

ዶክተር ቀደም በሚያውቋቸው የተሰጣቸው አሉታዊ የቅጽል ስምን ልክ በሚያሰኝ መልክ ግንቦት 7ን ደግፈው በፓል ቶኩ ሲለፍፉ የእይጥ ምስክሩ ድንቢጥ ሆነዋል ። ጦሩ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ እየተዋጋ ነው ሲሉ የሀሰት ምስክር ሰጥተዋል ።ማን ነገራቸው? ዋሾው ዶክተር ብርሃኑ መሆን አለበት ። ውስጠ አዋቂዎች በሞላ ውሸት ሲሉ እሳቸው በማንና በምን መረጃ ነው ጦርነት እየተካሄደ ነው የሚሉት ? ለጥቀውም ዶክተር ብርሃኑና አውቀዋለሁ፤ ተዋጊና አዋጊ ነው፤ደፋር ነው ብለው ማሾፍ በመሰል መልክ ተናግረዋል ፡፤ ይህ ደግሞ ዶክተር ብርሃኑን ሳይሆን ራሳቸውን ዶክተር ጌታቸውን ለትዝብት ይዳርጋቸዋል።'ስለሳቸውም የሜዳ ተሳትፎና ሚና ውስጠ አዋቂዎችን እንድጠይቅ ገፋፍቶኛልና በጉዳዩ የምመለስበት ይሆናል ። ዶክተር ብርሃኑ ግን ይህ ሙገሳ ስደት ለወሬ ያመቻል ይሆንባቸዋል ። ዶክተር ብርሃኑን የሚያውቁ (ለመሆኑ በትግል ሜዳ አብረው ነበሩ ከዶክተር ጌታቸው ጋር?የምታውቁ እስቲ ንገሩን) የግንቦት 7ኡ መሪ ከአፋቸው መንጣታት ውጪ የቀለህና ጥይት ጉዳይ ሲነሳ፤ የግንባር ተሳትፎ ሲነሳ ወገቤን የሚሉ ሽሽታምና ፈሪ መሆናቸውን ይናገራሉ ። ይህ ሀሰት ከሆነ እስቲ ዶክተር ብርሃኑ ከአስመራ ወደ ቨርጂኒያ መመመለሱን ትተው ጦሩን በግንባር እየመሩ ነጻ ሲያወጡን እንይ ! ዶክተር ጌታቸው እንደገና ዋሽተዋል ። በየጊዜው ትግልን በሚጎዳ መንገድ መዋሸትዎ ማንን ለምጥቀም ነው? ማንንስ ለምጉዳት ? ስምሪትዎስ በግልጽ ምንድነው ? ለነገሩ ፈሪ መሆን ያለ ነው፤ ፈሪ አይደለሁም አይደለም ብሎ ውሸት ነው ቀላልነት ።

ግንቦት 7ና መሪውን፤በዚያም አድርገው የኢትዮጵያን ጠላት ሻዕቢያን የሚደግፉ ጸረ ኢትዮጵያና በተጨማሪም ጸረ አማራ ግለሰቦችና ክፍሎች ናቸው ። ሻዕቢያ ጸረ አማራ በመሆኑ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ተገርዞ አርበኞች ግንባር ሆኖ ሳይረዳ እንዲያውም እየተቀጣ ጫጭቶ መቆየት የተገደደው ፡፤ የዶክተር ብርሃኑን ጸረ አማራ ስሜት ዶክተር ጌታቸውም በኦነግ አዳማቂነት ተጋርተዋል ። ራሱን የጠላ ምሁር ይሏል እርስዎ ኖት ማለት ነው ። የግንቦት 7ና የዶክተር ብርሃኑ ውሸት ውሎ አድሮ ሲጋለጥ እርስዎም ዶክተር ጌታቸው በህዝቡ ውድቅ፤ዋሾ፤ ከዜሮም ከቁጥር በፊት ያለ ዜሮ ይባላሉ ።

አይቀርም ። ወያኔ በትግልም ሆነ እርስ በርሱ ተናክሶ እንደሚጠፋው ሁሉ ።

የግንቦት7 አጭበርባሪነት ይጋለጥ!!

ለነዶክተር ብርሃኑ ዘረፋ አትመቹ !!